# ሰላት የተወ (የማይሰግድ) ሰው ፍርድ

ዝግጅት ፦ ሼኽ ሙሐመድ ቢን ሳሊህ አልዑሰይሚን
ትርጉም ፦ መሐመድ ሐሰን ማሜ

ምስጋና ለአላህ ይገባው ፤ የአላህ ሰላትና ሰላም በመልእክተኛችን ሙሐመድ፤ በቤተሰባቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን ።

ውድ ሙስሊም ወንድሜ ሆይ ! ይህ ለሼኽ ሙሐመድ ቢን ሳሊህ አልዑሰይሚን (አላህ ይዘንላቸውና ) የቀረበ ጥያቄና የሰጡት ምላሽ ነው ።

ጥያቄ ፦ አንድ ሰው ቤተሰቦቹን ሰላት እንዲሰግዱ ቢያዛቸውና ባይሰሙት : ከነርሱ ጋር አብሮ መኖር ነው ያለበት ወይንስ ቤቱን ለቆ መውጣት ?

መልስ ፦ እነዚህ ቤተሰቦች በጭራሽ የማይሰግዱ ከሆኑ ከሃዲያንና ከኢስላም የወጡ ናቸው ማለት ነው ። ስለሆነም ከእነሱ ጋር አብሮ መኖር አይችልም ። ነገር ግን ለነርሱ በተደጋጋሚ ጥሪ ሊያደርግላቸው ይገባል በርሱ ላይም ግዴታ ነው ። ምክንያቱም በቁርአን ፤ በሀዲስ፤ በሰሃቦች ንግግርና በትክክለኛው ሚዛን መሰረት ሰላት የተወ (የማይሰግድ)ሰው -አላህ ይጠብቀንና - ካፊር ነውና ።

<u>ቁርአናዊ ማስረጃ</u>

አላህ ሙሽሪኮችን(በአላህ ላይ የሚያጋሩትን) በማስመልከት እንዲህ ብሏል :

" فَإِن تَابُوا وَأَقَامُوا الصَّلَوٰةَ وَءَاتَوُا الزَّكَوٰةَ فَإِخْوَانُكُمْ فِي الدِّينِ " التوبة 11.

" ከተፀፀቱ ፤ሰላትንም ከሰግዱ ዘካንም ከሰጡ የሃይማኖት ወንድሞቻችሁ ናቸው "
አት_ተውባህ_11

አንቀጹ የሚያስገነዝበው ቁም ነገር እነዚህን ተግባራት ካልፈፀሙ ወንድሞቻችን እንደማይሆኑ ነው ። እስላማዊ ወንድማማችነት ከኢስላም በሚያስወጣ የክህደት ተግባር ቢሆን እንጂ በማንኛውም ትልቅ ወንጀል ቢሆንም እንኳ በቀላሉ አይፈርስም ።

<u>ሃዲሳዊ ማስረጃ</u>

የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም)እንዲህ ብለዋል :

" بَيْنَ الرَّجُلِ وَبَيْنَ الكُفْرِ وَالشِّرْكِ تَرْكُ الصَّلَاةِ " رواه مسلم .

" በሰውየውና በክህደት እንዲሁም በማጋራት መካከል ያለው ልዩነት ሰላት ነው"
(ሙስሊም ዘግበውታል): ቡረይዳህ (ረድየ ላሁ ዐንሁ)ባስተላለፈው ሀዲስ ላይም እንዲህ ብለዋል -:

" العَهْدُ الذِّي بَيْنَنَا وَبَيْنَهُمُ الصَّلَاةُ ، فَمَنْ تَرَكَهَا فَقَدْ كَفَرَ " رواه الترمذي ، وقال : حديثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ.

:" በእኛ እና በእነርሱ(በከሃዲያን)መካከል ያለው መለያ (ቃል ኪዳን) ሰላት ነው ፤ (ሰላትን)የተወ በእርግጥም ከደ፞ል " (አት_ቲርሙዚ ዘግበታል)

የሰሃቦች ንግግር

ይህን አስመልክቶ ከሰሃቦች አንደበት የተነገሩ መልእክቶች በርካታ ናቸው :

_ ዑመር (ረድየ አላሁ ዐንሁ) እንዲህ ብሏል፡-

" لاَ حَظَّ فِي الإِسْلاَمِ لِمَنْ تِرَكَ الصَّلاَةَ " .

: " ሰላት የተወ ሰው በኢስላም ውስጥ ምንም እድል (ድርሻ ) የለውም:: "

እድል(ድርሻ ) የሚለው ቃል ጥቅል ቃል ነው :: ስለሆነም አነሰም በዛም በኢስላም ውስጥ ምንም አይነት ቦታ እንደሌለው ያስረዳል።

_ ዐብዱላህ ኢብኑ ሸቂቅም ( ረድየ አላሁ ዐንሁ ) እንዲህ ይል ነበር፡-

" كَانَ أَصْحَابُ النَّبِيِّ ﷺ لاَ يَرَوْنَ شَيْئًا مِنَ الأَعْمَالِ تَرْكُهُ كُفْرٌ غَيْرَ الصَّلاَةِ "

" የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦች ቢተው (ቢቀር) ክህደት ነው ብለው ከሰላት ውጭ የሚቆጥሩት ነገር አልነበረም "

ከትክክለኛው አእምሯዊ ሚዛን አንፃር

ከትክክለኛ አእምሯዊ ሚዛን አንፃርም ስንመለከተው ማንኛውም በልቡ ውስጥ ቅንጣት ያክል ኢማን ያለው ሰው የሰላትን ደረጃና አላህ የሰጠውን ቦታ እያወቀ ሰላትን እርግፍ አድርጎ ይተዋል ተብሎ ይታሰባልን？！በፍፁም

_ ሰላት የተወ (የማይሰግድ) ካፊር አይባልም ( ከኢስላም አይወጣም) ያሉት እንደ ማስረጃነት ያጣቀሷቸውን ሳስተውል ከአራት ሁኔታዎች እንዳማይወጣ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡-

1_ በመሰረቱ ለተባለው ጉዳይ አስረጅ አይደለም

2_ ሰላትን መተው እንደማይገባ በሚያመላክት ባህሪ(ገለፃ)የተገደበ ይሆናል

3_ አንዷን ሰላት በመተው ዑዝር () በመስጠት ላይ የተገደቡ ናቸው

4_ ሰፊ መልእክት ያላቸው ይሆኑና ክህደት ( ኩፍር) መሆኑን በሚያረጋግጡ አንቀፆች የተገደበና የተብራራ ይሆናል

ሰላት የማይሰግድ ካፊር(ከሃዲ) እንደሆነ ግልፅ ከሆነ ፤ ከኢስላም የወጡ ሰዎች ህግጋት ይመለከተዋል ማለት ነው።

(ሰላት የማይሰግድ ሙእሚን ነው፤ ጀነት ይገባል፤ከእሳት(ከቅጣት) ነፃ ይወጣል እና የመሳሰሉትን የሚያመለክት ማስረጃ የለም። በመሆኑም ሰላት የማይሰግድ " ከሀዲ ነው " የሚለውን "ፀጋን መካድ" ማለት ነው አልያም "መለስተኛ ክህደት ነው" ወደሚለው ግንዛቤ እንድንጓዝ አያደርገንም ።)

እንዲህ ከሆነ የሚከተሉት ህግጋቶች ይመለከቱታል ፡-

አንደኛ፡ አይዳርም(እርሱን ማጋባት አይቻልም ) ፡የማይሰግድ ሆኖ የጋብቻ ውል ቢፈፀም ጋብቻው ትክክል አይሆንም ፡በዚህ ውልም ባለቤቱ አትፈቀድለትም ምክኒያቱም አላህ (ﷺ)የተሰደዱ ሴቶችን አስመልክቶ እንዲህ ብሏልና፡-

“ فَإِنْ عَلِمْتُمُوهُنَّ مُؤْمِنَاتٍ فَلاَ تَرْجِعُوهُنَّ إِلَى الكُفَارِ لاَ هُنَّ حِلٌّ لَهُمْ وَلاَ هُمْ يَحِلُّونَ لَهُنَّ " الممتحنة – 10.

" አማኝ መሆናቸውን ካወቃችሁ ወደ ከሃዲያን አትመልሷቸው (ምክኒያቱም) እነርሱ (ሴቶቹ)ለእነርሱ(ለወንዶቹ) የተፈቀዱ አይደሉምና፡እነርሱም (ወንዶቹ) ለእነርሱ አይፈቀዱምና " አልሙምተሒና 10

ሁለተኛ፡ የጋብቻ ውል ከተፈፀመ በኋላ ሰላት ቢያቆም (ቢያቋርጥ)ጋብቻው ይፈርሳል፤ ባለቤቱም ለእርሱ የተፈቀደች አትሆንም ። ለዚህም ማስረጃ ያለፈው አንቀፅ ነው ።

ሦስተኛ፡ ይህ ሰው ቢያርድ እርዱ አይበላም ። ለምን ? ከተባለ ? ክልክል ስለሆነ ነው መልሳችን ። በአንፃሩ ደግሞ አንድ አይሁዳዊ ወይም ክርስቲያን ያረደውን መብላት ይፈቀድልናል ። በዚህም የተነሳ የዚህ ሰውዬ እርድ _አላህ ይጠብቀንና _ ከአይሁድና ከክርስቲያን እርድ የከፋ ይሆናል ማለት ነው ።

አራተኛ፡ መካ ወይም የመካን ክልል አልፎ መግባት አይፈቀድለትም ። ምክኒያቱም አላህ(ﷺ)እንዲህ ብሏልና፡-

" يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنَّمَا المُشْرِكُونَ نَجَسٌ فَلاَ يَقْرَبُوا المَسْجِدَ الحَرَامَ بَعْدَ عَامِهِمْ هَذَا " التوبة 28.

" እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አጋሪዎች እርኩሶች ናቸው። ከዚህም ዓመታቸው በኋላ የተከበረውን መስጊድ አይቅረቡ። " አት_ተውባህ፡28

አምስተኛ፡ ከዘመዶቹ አንዱ ቢሞት ውርስ የመካፈል መብት የለውም። ለምሳሌ ፡- አንድ ወላጅ ሰላት የማይሰግድ ልጅ (ወላጅ ሙስሊም ሆኖ ሰጋጅ ነው ልጁ ግን ሰጋጅ አይደለም) እና ራቅ ያለ የአጎት ልጅ ጥሎ ቢሞት ማነው ሊወርሰው የሚገባው ? ከተባለ

መልሱ: ወራሽ የሚሆነው የገዛ ልጁ ሳይሆን የአጎቱ ልጅ ነው ። ምክንያቱም የአላህ መልእክተኛ ኡሣማህ ባስተላለፈው ሀዲስ ላይ እንዲህ ብለዋል ፡-

" لاَ يَرِثُ المُسْلِمُ الكَافِرَ وَلاَ الكَافِرُ المُسْلِمَ" متفق عليه .

" ሙስሊም የሆነ ከሃዲን አይወርስም ፤ ከሃዲ የሆነም ሙስሊምን አይወርስም። " (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)እንዲህም ብለዋል ፡-

" أَلْحِقُوا الفَرَائِضَ بِأَهْلِهَا ، فَمَا بَقِيَ فَلِأَوْلَى رَجُلٍ ذَكَرٍ " متفق عليه .

“ ውርስን ለሚገባው አድርሱ የተረፈውን ቅርብ ለሆነ ወንድ ወገን ስጡ ” ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል ።

ይህ እንደ ምሳሌ የተጠቀሰ ሲሆን ወራሾችን ሁሉ የሚመለከት ነው።

ስድስተኛ፡ ቢሞት ሬሳው አይታጠብም ፤ አይገነዝም ፤ አይሰገድበትም፤ ከሙስሊሞችም ጋር አይቀበርም ። ምን ይደረግ ከተባለ ፡ ጭር ያለ ስፍራ ይወሰድና ጉድጓድ ተቆፍሮ ከነልብሱ እንቀብረዋለን ። ምክንያቱም ለየት ያለ ክብር የለውምና። በዚህም መሰረት ማንኛውም ሰው የማይሰግድ ዘመድ ከሞተበት መስጅድ አምጥቶ ማሰገድ አይፈቀድለትም ።

ሰባተኛ፡ የቂያማ ቀን ከክህደት መሪዎች ማለትም ከፊርዐውን፡ከሃማን፤ ከቃሩንና ከኡበይ ኢብኑኸለፍ ጋር አብሮ ይቀሰቀሳል ። ጀነትም አይገባም ፡ ቤተሰቡም ማንም ቢሆን እዝነትንና ምህረትን ሊማፀኑለት አይገባም ። ምክንያቱም ከሃዲ ነው ፤ እንዲሁም አላህ እንዲህ ብሏል ፦

" مَا كَانَ لِلنَّبِيِّ وَالَّذِينَ آمَنُوا أَن يَسْتَغْفِرُوا لِلْمُشْرِكِينَ وَلَوْ كَانُوا أُولِي قُرْبَى مِن بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُمْ أَنَّهُمْ أَصْحَابُ الْجَحِيمِ " التوبة 113.

" ለመልእክተኛውም ይሁን ለማንኛውም አማኝ የእሳት ጓድ መሆናቸው ግልፅ ከሆነላቸው በኋላ የቅርብ ዘመድ ቢሆኑም እንኳ ለሙሽሪኮች ምህረትን ሊጠይቁላቸው አይገባም ።" (አት_ታውባህ 113) .

ውድ ወንድሞቼ ጉዳዩ እጅግ አንገብጋቢና አደገኛ ነው። ከመሆኑም ጋር በጣም የሚያሳዝነው አንዳንድ ሰዎች ይህን ጉዳይ ችላ በማለት የማይሰግድ ሰው እቤታቸው ያስቀምጣሉ ነገሩ ከልክል ሆኖ ሳለ ።

## ሰላት የተወ ሰው ወንድም ሆነ ሴት ፍርዱ ይህን ይመስላል

ሰላትን የተውክና የዘነጋሃት ሆይ ! የቀረውን እድሜህን መልካም ሥራ በመስራት ተጠቀምበት ፡ ከእድሜህ ምን ያክል እንደቀረህ አታውቅምና ወራት ፤ ቀናት ፤ ሰዓታት ?

የዚህ ሁሉ እውቀት አላህ ዘንድ ብቻ ነው።

ቀጥሎ ያለውን የአላህ ቃልን ዘውትር አስታውስ ፡

" إِنَّهُ مَن يَأْتِ رَبَّهُ مُجْرِمًا فَإِنَّ لَهُ جَهَنَّمَ لاَ يَمُوتُ فِيهَا وَلاَ يَحْيَى " طه - 74

" እነሆ ከሃዲ ሆኖ ወደ ጌታው የሚመጣ ሰው ለእርሱ ገሀነም አለችለት ፤ በውስጧም አይሞትም ህያውም አይሆን "ጣሃ 74

እንዲህ የሚለውንም ቃል አስታውስ ፡

{فَأَمَّا مَنْ طَغَى (37) وَآثَرَ الْحَيَاةَ الدُّنْيَا (38) فَإِنَّ الْجَحِيمَ هِيَ الْمَأْوَى (39)} [النازعات: 37 - 39]

" የካደ ሰውማ ፤ ቅርቢቱንም ህይወት የመረጠ ፤ ገሀነም እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት " አልናዚዓት ፡ከ 37_39

አላህ ለመልካም ነገርና ለጥሩ እድል እንዲያበቃህ ፤ እንዲሁም የተቀረውን እለትህን በእውቀት፤ በስራና በዳዕዋ በሸሪዓ ጥላ ስር የምታሳልፍ ያድርግልህ ስል እማፀነዋለሁ

# ወሰለላሁ ዓላ ነቢዩና ሙሀመዲን ወዓላ ኣሊሂ ወሰሕቢሂ ወሰለም